# ፀሐይ, ጨረቃ እና ንፋስ



Amharic

ፀሐይ, ጨረቃ እና ንፋስ

ፀሐይ, ጨረቃ እና ንፋስ

ጸሓፊ፡ ኴትሶ ራኖኦሲ

ስዕላዊ መግለጫዎች፡ የፓሌንግ ልጆች

በኮሀሶ ራኖሲ እና ማሪዎን ድሪዉ የተተረጎመ

# ፀሐይ, ጨረቃ እና ንፋስ

Amharic
Ethiopia

Copyright © 2025, SIL Ethiopia

http://creativecommons.org/licenses/by-nc-sa/4.0/
You may not use this work for commercial purposes. You may adapt and add to this work, but you may distribute the resulting work only under the same or similar license to this one. You must keep the copyright and credits for authors, illustrators, etc.

Writer: Khothatso Ranoosi
Illustration: Children of Paleng
Translated By: Biruktawit Girma

ከረጅም ጊዜ በፊት ፣ ፀሐይ ፣ ጨረቃ ፣ ዝናብ እና ንፋስ ይጣሉ ነበር።



ችግሩ ፀሐይ ቀኑን ሙሉ ለማብራት ፈለገች። ጨረቃ በየቀኑ ብርሃኗን መስጠት ፈለገች። ዝናብ በየቀኑ መዝነብ ፈለገ፤ ንፋስ ደግሞ በየቀኑ መንፈስ ፈለገ። አንዳቸው ለሌላው እድል መስጠት አልፈለጉም።



አብረው ተቀምጠው ስለ ጉዳዩ ለመነጋገር ወሰኑ። ፀሐይ፤ ጨረቃን እንዲህ ስትል ጠየቃቻት "ምድርን የሚረዳ ምን ታደርጊያለሽ?" ጨረቃም እንዲህ ስትል መለሰች፤ "እንስሳት ማደን እንዲችሉ በምሽት አበራለሁ።"



ጨረቃ፤ ዝናብን እንዲህ ሲል ጠየቀች፤ "ምድርን የሚረዳ ምን ታደርጋለህ?" ዝናብ መለሰ፤ "ዛፎች እና ተክሎች በደንብ እንዲያድጉ ለምድር ውሃ እሰጣለሁ። ለእንስሳት የመጠጥ ውኃ እሰጣለሁ"



ዝናብ፣ ንፋስን እንዲህ ሲል ጠየቀ፤ "ምድርን የሚረዳ ምን ታደርጋለህ?" ንፋስም መለሰ፤ "ምድርን በመጥረግ ንፁህ እጠርጋለሁ። ዝናቡንም በምድር ሁሉ ላይ እበትናለሁ።"



ንፋስ፣ ፀሐይን እንዲህ ሲል ጠየቀ፤ "ምድርን የሚረዳ ምን ታደርጊያለሽ?" ፀሐይም መለሰች፤ "እንስሳትና ተክሎች እንዲኖሩ ለምድር ብርሃን እና ሙቀት እሰጣለሁ።"



ፀሀይ፣ ጨረቃ፣ ዝናብ እና ንፋስ በጥሞና እርስ በእርሳቸው ተደማመጡ።



ከዚያም ፀሐይ "እውነት ነው እያንዳንዳችን ምድርን በየራሳችን ልዩ መንገድ እንረዳለን።" "አዎ፣ አለች ጨረቃ "ከመካከላችን አንዱ ከሌላው የተሻለ አይደለም።" "አብረን መስራት እንችላለን" አለ ዝናብ። ንፋስም "እንግዲያስ ቀኖቹን እንካፈል" አለ። ሁሉም ተስማሙ።



ለዛም ነው አንዳንድ ጊዜ ፀሀይ ስትወጣ
ጨረቃን የምናየው። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ
ዝናብ በሚዘንብበት ጊዜ ነፋሱ ይሰማናል።
ፀሀይ፣ ጨረቃ፣ ዝናብ እና ንፋስ አብረው
በደንብ ይሰራሉ። እርስ በርሳቸውም
ይግባባሉ/ይረዳዳሉ።



ፀሀይ ፣ ጨረቃ ፣ ዝናብ ወይም ንፋስን ትወዳለህ/ሽ? በጣም የምትወደውን/የምትወጂውን ሳል/ሳይ።

መኖር እንድንችል ምድር ታስፈልገናለች። ምግብ፣ መጠለያ፣ እንስሳትና ዕፅዋት ትሰጠናለች። እነዚህ ሁሉ በሆነ መንገድ ይረዱናል። በምላሹ፤ ሁላችንም ምድራችንን ለመርዳት የሆን ነገር ማድረግ እንችላለን። ምድርን ለመርዳት ምን ታደርጋለህ/ሽ? ፃፈው/ፊው።

Let's grow a library
Bloom®